## ግልጽ ደብዳቤ ለአቶ ተስፋዬ ገብረአብ

ይድረስ ለአቶ ተስፋዬ ገበረ አብ ቀደም ሲል የወያኔ ሹመኛ ለነበሩት፣

በቅድሚያ ልባዊ ሰላምታዬን ተቀበሉኝ፡፡ በጤና ከርመዋል ብዬ በጠይቅዎት እወዳለሁ፡፡ መቸም ከሩቅ ሁኜ ሳስበው ስደት ከቶውንም ጤና ይሰጥ አይመስለኛም፡፡ እንደው እንደ አንዳንዶች በስደት ስም ሌላ አስነዋሪ ሥራ የሚሠሩ፣ "ስደት አልጋ ባልጋ ነው!" ቢሉ ልንገረም ቀርቶ ጆሮ ልንሰጣቸው አይገባም፡፡ ብቻ የርሶን ደህንነት ብዙዎች የሚረዱት ይመስለኛል፡፡ በቅርቡ የመንግስቱን መፀሐፍ አስመልክተው እወቅሁ ብለው የለቀቁትን ልቅ በቅጡ አየሁትኝ፡፡ በዚህም ጤናዎን ተረዳሁት፡፡ ይበሉ ወደ ተነሳሁበት ላቅና፡፡

በአክብሮት የምጠራዎ ከእርሦ በእድሜ በጣም ልጅ ሆኜ ሳይሆን ትህትናይን ለማሳየት ነው፡፡ በዚህ ደብዳቤዬ የማነጋግሮት የፋሽስቱ የመንግስቱ ኃ/ማርያም መፀሐፍን አስመልክተው የሰነዘሩት ነገር ጠቅ ስላደረገኝ ነው፡፡ በጽሁፎት ላይ ስለ ኢህአፓ የመጀመሪያ ምንጭዎ ነፍሳቸውን ይማረውና እናትዎ በመሆናቸው እኔም እጋራውወታለሁ፡፡ እኔ በዚያ ዘመን በጣም ትንሽ ስለነበርኩ የኢህአፓን ጠረን ለማሽተት አልታደልኩም፡፡ ካደኩ በኃላ ግን የኢህአፓ ልሳን የሆነውን ዴሞክራሲያ ን በተለያየ አጋጣሚ ማንበብ ችያለሁ፡፡ በተለይ ደግሞ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪ በነበርኩበት ወቅት ከጥናት ጋር በተያያዘ በርካታ ቅጾችን ማንበብ ታድያለሁ፡፡ ይህን ስልዎት በወቅቱ የነበሩትን እንደ የሰፊው ህዝብ ድምጽ ዓነቶቹን ሁሉ ዓይቻለሁ፡፡ በዚህ ምናልባት ከእርሦ ጋር እንለያይ መሰለኝ፡፡ በሌላ አንጻር የእኔም እናት ዛሬ እማሆይ ሆናለች። ስለ ኢህአፓ በርካታ ቁም ነገሮችን አስጨብጣኛለች፡፡ እናቴ እንዳለ ችኝ  በየሰፈሩ የተማረ የሚባል ሰውና ተማሪዎች በአብዛኛው ኢህአፓዎች ነበሩ፡፡ አንዴ በሁዳዴ ጾም አስቀድሰው፣ ከቤተክርቲያን ወጥተው ሲሄዱ፣ የሂሩት እናት የሚባሉ ጓደኛዋ ልጅ፣ ኢዮብ የሚባል ገድለውት እግሮቹን በገመድ አስረው ሲጉትቱት አይታ ለእረጅም ጊዜ አራሷን ስታ እንደነበር አስታውሳለሁ፡፡ እንዴ ደግሞ ማለዳ ኪዳን ለማድረስ ወደ ቤተክርስቲያን ስትሄድ አስካለ የምትብል እግሮቿ በግርፋት የነፈሩ፣ ጀርባዋ በእሳት የተጠበሰ፣ ጡቶቿ በስለት የተሰነጠቁ፣ ገድለዋት እላይዋ ላይ "ቀይ ሽብር ይፋፋም!" የሚል ወረቀት ለጥፈው፣ እዋናው መንገድ ላይ አስከሬንዋን ጥለው፣ ተላላፊውን ሰው ሁሉ እምባውን ወደ ሆዱ አስፈሰሱት፡፡ በዚያ ዘመን ልጅዋ የሞተባት እናት ቤትዋን ዘግታ በነጠላዋ ፊትዋን ሸፋፍና ታነባ እንደነበር እማዬ አጫውታኛለች፡፡ በመንግስቱና አራጆቹ ልጅዋ የተገደለባት እናት ድምጧን አውጥታ ማልቀስ ተከልክላ ነበር፡፡ ከዚህ በተረፈም መከራው የእኛን ቤተሰብም ቀጥፎብናል፡፡ አባቴን፣ እህትና የእናቴን ሁለት ወንድሞች አጥቻለሁ፡፡ አክስቴና አንደኛው አጎቴ በወቅቱ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ነበሩ፡፡ ቤተሰቦቻችን፣ ዘመድ አዝማዶቻችንና ጎረቤቶቻችን አንስተው አይጠግቧቸውም፡፡ በትህትናቸውና በሰው አክባሪነታቸው እስከ ዛሬ ሲያነሷቸው የቱን ያህል መልካም እንደበሩ እየተማርኩ ነኝ፡፡ እየውልህ ሞተውም ሦስት አስርተ አመታት እንኳን አልፏቸው አልተረሱም፡፡ በጎ ምግባር ከመቃብር በላይም ያስጠሯል ነው፡፡ እመዬ እስከ ዛሬ የዚያን ጊዜ የኢህአፓን ልጆች እያነሳች ታጫውተኛለች፡፡

ከናቴ ለጥቆ ስለኢህአፓ ብዙ ያወቅሁት አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪ በነበርኩበት ወቅት ነበር፡፡ በአጋጣሚ በትምህርት ክፍልም ሆነ በመኝታ ቤት ጥቂት ተማሪዎች የዛን ዘመን መከራ ያሳለፉ ስለነበሩ ኢህአፓንና የኢህአፓን ልጆች በደንብ ከቀጥተኛው መረጃ ማግኘት ታድያለሁ፡፡ እርስዎ ከታሪኮ እንደተረዳሁት በዩኒቨርሲቲ ዓለም ውስጥ ለማደግ አልታደሉምና ይህን እድል አጥተውታል፡፡ ጽሁፎን ሳየው በጣም አሳዘኑኝ፡፡ እርሶ በትገሬነትዎ የወያኔ ሹመኛ ካድሬ ሆነው እጆችንና ህሊናዎን በወያኔ ወንጀል ነክረው ዛሬ እራሶን እንደ ትልቅ ሰው፣ ማለቴ ንጹህ አድርገው፣ ያዙኝ ልቀቁኝ ሲሉ አለማፈርዎ አይገርመኝም፡፡ በእኔ እድሜ እንደርሶ የመሰሉ አንገተ ቢሶች ብዙ አይቻለሁና ነው፡፡ አቶ ተስፋዬ! እንደው ለመሆኑ ስብህት ነጋን ሰለ ኢህአፓ ዋቢ አርገው መጥቀስዎ በጣም ተሰምቶኛል፡፡ ለኔ ስብሀትና የደርግ ሹመኞች አንድ ናቸው፡፡ ከሁለቱም ወገኖች ኢህአፓን በተመለከተ እውነት ይነገራል ብሎ መጠበቅ ተላላነት ብቻ ሳይሆን የግፈኞች ፕሮፓጋንዳ

ሰለባም መሆን ይመስለኛል፡፡ እንዲህ አይነት ነገር ልቤን ያደማዋል፡፡ በበኩሌ ጋዜጣም ይሁን መጽሔት ስለ ኢህአፓ በጎም ይሁን ክፉ ይዞ ከወጣ አያመልጠኝም፡፡ እሰከ ዛሬም ኢህአፓን የተመከተ ርዕስ የያዘ ጋዜጣም ይሁን መጽሔት ገበያው የሰፋ ነው፡፡ እርስዎ የወያኔ ባለስልጣን በነበሩበት ወቅት የኢህአፓን ጉዳይ የያዙ ጋዜጦችና መጽሔቶች ከመደበኛ ዋጋቸው በሦስትና በአራት እጅ ጨምረው ይሸጡ እንደነበር የሚሳት አይመስለኝም፡፡

ኢህአፓን እንደተረዳሁት ኢትዮጵያንና ህዝቧን ከልብ ይወዳል፡፡ ኢህአፓ በሀገርና በህዝብ ላይ ሸፍጥ እንደማያውቅ ከታሪኩ ተገንዝቤያለሁ፡፡ በዚህ ጽናቱ በርካታ ተፃራሪዎች እንደተፈጠሩበት ይታወቃል፡፡ ይህን ለእርስዎ የእፎይታ አዘጋጅ ለነበሩት "ጋዜጠኛ" መንገር እንኳ ተገቢ አይሆንም፡፡ የኢህአፓን ስምና ዝና ለማጥፋት የሚማስኑ እንዳሉም ለእርስዎ ቀደምት የወያኔ ሎሌ መንገሩ ሌላ ያስመስልብኛል፡፡ ኢህአፓን ደርግ ኢሠፓዎች፣ ወያኔ ኢህዴጎች፣ ዘረኛ ጎጠኞች፣ ከኢህአፓ የወጡ ከሀዲዎች አምርረው ይጠሉታል፡፡ የሆነ ያልሆነውን ይለጥፉበታል፡፡ ደርግ በአስራ ሰባት የግዛት ዘመኑ በየአጋጣሚው ሁሉ ኢህአፓን ለማስጠላት ያልደረደረው ውንጀላ አልነበረም፡፡ ደርግ ሞተ፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብም ተደሰተ፡፡ በደርግ እግር የተተካው ወያኔም በኢህአፓ ላይ የጥላቻ ዘመቻን ከደርግ ባልተናነሰ መልኩ ቀጠለ፡፡ ይህ እንዳልያዘለት ሲረዳው ኢህአፓ ሞቷል ብሎ ተፈጠመ፡፡ የኢህአፓ ገዳይ እንደሆነም አቅራራ፡፡ እዚች ላይ እርሶም የድርሻዎን ያንሱ፡፡ በረከትና ጓደኞቹ አንዴ ገደልነው፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ወረስነው እያሉ ይዘላብዱ በነበረበት ውቅት፣ እርሦም ተላላነት ሳይጫንዎ እንዳልቀረ ይሰማኛል፡፡ ወያኔም ሃያ አመት በኢህአፓ ላይ ዘመቻውን ቀጠለ፡፡ ኢህአፓ ግን እየታገለ እንደሚገኝ ዓለም ያወቀው ታሪክ የመዘገበው መሆኑ ላይ እስጥ አገባ አያሻውም፡፡ እስኪ አንዴ ስሙኝ! ወያኔ የኢህአፓ መሪዎችነ እነ ፀጋዬ ደብተራውን አስሮ፣ አንዴ የጦር ምርከኞች ናቸው፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ አላሰርኳቸውም፤ በውጊያ ላይ ሞተዋል፤ ይለን ነበር፡፡ እርሦ ስልጣን ላያ በነበሩበት ወቅት ይህንን አላውቅም ቢሉኝ አይገርመኝም፡፡ ግን እኔ እንደኔ እውነቱ ይሻሎታል፡፡ ደብተራውን እስር ቤት እንዳዩት መግለጽዎ ደስ አለኝ፡፡ ልክ እንዳሰብኩት ሥየ ፣ ተወልደ፣ ገብሩ፤ ጻድቃን፣ ከወያኔ ተኳረፈው ከተገፈተሩ በኃላ ስለ እነ ደብተራው አንዴም አለመተንፈሳቸው፣ ዛሬም የወያኔ ርኩስ መንፈስ እንደተጸናወታቸው ሳስብ፣ እራሳቸውን በገዛ ፈቃዳቸው የሀሰት ባሮች እንዳደረጉ ይሰማኛል፡፡ ደብተራውና ጓደኞቹን ለጉድጓድ እስር የዳረገው ወያኔ የጭራቁ መንግስቱ ኃይለ ማርያምን ሹማምንት በምህረት ለቀቀ፡፡ እኔ በበኩሌ እርሦም አሁን በአጋጣሚ፣ ያውም እንደ ዘበት የነደብተራውን ጉዳይ ማንሳቶ ምንዓይነት ሰው እንደሆኑ ቢያሳየኝም እርሶንም አጋጣሚውንም አመሰግናለሁ፡፡ ደብተራው የደብረ ዘይት ልጅ ነበር፡፡ ስለእሱ ሳያውቁ ማደግዎ ይገርማል፡፡ በጽሑፎ የኢህአፓን ታሪክ ለመጻፍ ማሰብዎን ነግረውናል፡፡ የኢህአፓን ታሪክ ለመጻፍ ህሊና አቅም፣ ጽናትና አስተንታኝና አመዛዛኝ ህሊና ይጠይቃልና ቆም በለው ቢያስቡበት ደግ ነው፡፡ አንድ በኢህአፓ ስም የተጻፈ ያ ትውልድ የተሰኘ መፀሐፍ ደራሲ የሆኑት አቶ ክፍሉ ታደሰ የጻፉልን የድርጁትን ታሪክ ሳይሆን የአመራሩን ታሪክ በተለያ የራሳቸውን ውዳሴ ነው፡፡ የሚገርመው በዚህ መፀሐፍ ውስጥ አንዴ በ1969 ዓ.ም. ሌሊት ክፍሉ ደጃች ውቤ መቀመጫቸው ላይ በጥየት ተመትተው፣ ደማቸው እየፈሰሰ ማንም ቁም ሳይላቸው ወደ መርካቶ መጓዛቸው፣ አይነ ግንባሩን ቢጨፍን አይነ ልቡናውን መጨፈን አለመቻሉን ነው፡፡ እኔ እንኳን ዛሬ ልጅም ሆኜ ከእውነት የራቁ ፊልሞችን ማየት አልወድም፡፡ ክፍሉ ኢህአፓዎች ዝም ቢሏቸውም እንደኔ አይነቱ ኢህአፓን ከእናቱ አፍ የተማረውን ግን ይሰነፍጠዋል፡፡

እርሶም ታሪኩን እጽፋለሁ ያሉትን ጉዞ ከመጀመርዎ በፊት እንደ ኩሬ ውሀ ረጋ በለው ዙርያ ገባውን ይመዝኑት ብዬ ብመክርዎ ከመዳፈር አይቁጠሩብኝ፡፡ ጽሑፎን ለመጻፍ ያበቃዎት የመንግስቱ ኃይለ ማርያም መፀሐፍ በድረ,ገጽ መሰራጨቱ እንዳንገበገበዎት ተረድቻለሁ፡፡ እኔ በዚህ ሀሳብዎ በጣም አልስማማም፡፡ አይክፋዎት፡፡ እርሶ እንዳሉት ያሰራጨው ኢህአፓ ከሆነ በበኩሌ ላመሰግለው እወዳለሁ፡፡ ግን አልመስልህ አለኝ፡፡ ለምን ቢሉ ድፍን አስራ ሰባት አመት በኢህአፓ ላይ የዘመተ ሰው-በሌ ጭራቅን መፀሐፍ በማሰራጨቱ ከሚጠቀመው

የሚጎዳው ይብስ አይመስለኝም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ እንደኔ መፀሐፉን ማግኘት ለማይችል አጋጣሚው እንዴት ደስ ይላል፡፡ በሌላ በኩልም መንግስቱ አይጎዳም ላሉት በደምብ ይጎዳል፡፡ ጉዳቱ በአንካሴም ባይሆን ይገዘግዛል፡፡ ሌላው ደግሞ ለአሳታሚው ለአሳታሚው ዓይኖቻችን ጨምቀውለታል፡፡ ለእንዲህ አይነት አሳታሚም ትማህርት ሰጪነቱ በቀላሉ ሊታይ አያገባውም የሚል ሀሳብ አለኝ፡፡ እንዲህ አይተነቱ አሳታሚ የመንግስቱን መፀሐፍ ለማሳተም የተጓዘበት መንገድ ለሀገሬ ኢትዮጵያና ለህዝቧ የሚበጅ አይደለምና እንዲታረሙም ማስጠንቀቂያነቱ በቅጡ ሊታይ ይገባዋል፡፡ እርሦ አፍዎን ሞልተው መንግስቱ እንደማይጎዳ ቢነግሩንም፣ እኔ እንክት አድርጎ እንደሚጎዳው ልነግርዎ እወዳለሁ፡፡ ኢህአፓ ለመንግስቱ ምላሽ አልሰጠም የሚሉትም ስለ አገርዎ ያሎት ተቆርቋሪነት ጠንገር ማለቱን አሳይቶኛል፡፡ ለመሆኑ ባቢሌ ቶላ ጽፎት በፀጋየ ገብረ መድህን የተተረጎመው "አንድ ትውልድ ለመምተር ቀዩ ሽብር በኢትዮጵያ"ን አንበበውት ይሆን ብዬ እራሴን ጠየቅሁ፡፡ ምንም እንኳን ይህ መጸሐፍ በ1989 ዓ.ም. ለንባብ ቢበቃም፣ ለመንግስቱ መጸሐፍና ለሌሎችም ቋሚ መልስ የሚሰጥ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡ ከላነበቡት ወይም በግልብ አንብበውት ከሆነ አሁን ጫን ብለው ያንብቡት፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ህሊናዎን ወደ ኋላ ቀለስ አድርገው እናትዎ የነገርዎትን ደግመው መስመር በመስመር ያንብቡት፡፡ እናትዎ ያልዎት እውነት ነው፡፡ እርስዎ ባሉበት በሰከነ መልኩ ልወቅ ካሉ እድሉ አሎትና ይሞክሩ፡፡

መንግስቱ እህቶቼ ብልት ውስጥ የጋለ ብረት የጨመረ፣ የእህቶቼን ጡት በሲጋራ እሳት ያነፈረ፣ የእህቶቼን ከንፈሮች በሲጋራ እሳት የጠበሰ፣ የወንድሞቼን ጥፍርና ጥርስ በፒንሳ የነቀለ፣ የወንድሞቼን ብልት በኮርባጅ የገረፈ፣ የወድሞቼንና የእህቶቼን ጀርባ በእሳት የጠበሰ፣ በቁመናቸው ሥጋቸውን በሳንጃ የሰነጠቀ፣ የጎመደ፣ የወንድሞቼንና የእህቶቼን እግሮች በግርፊያ ሥጋቸው እረግፎ፣ በአጥንት ብቻ ያስቀረ፣ በሽቦ እያነቀ የገደለ፣ እህቶቼንና እናቶቼን የደፈረ፣ ያስደፈረ፣ ወንድሞቼንና እህቶቼን የኢላማ ተኩስ መለማመጃ አድርጎ ያስገደለ፣ አስከሬናቸውን በመሬት ላይ እንዲጎተት ያደረገ፣ ወንድሞቼና እህቶቼን ካስገደለ በኋላ ለተገደሉበት ጥይት ገንዘብ ያስከፈለ፣ ወላጆች ድምጻቸውን አውጥተው እንዳያለቅሱ የከለከለ፣ ወንድሞቼ ጀርባ ላይ ድንጋይ አስሮ ወንዝ በመጣል በአዞ ያስበላ፣ ብቻ በአጠቃላይ የሰው ልጅ ሊፈጽማቸው፣ ቀርቶ ሊያስባቸው የሚከብዱ ስየሎችን የፈጸመ ነውና ለመንግስቱና ለጫማ ላሾቹ መቆርቆርዎን ቢያቆሙ ደስ ያለኛል፡፡ ጽሑፎን ለእመየ አንብቤላት በጥኑ አዝናቦታለች፡፡ የእናትዎም ቃል ከመቃብራቸው በላይ ነውና አይዘንጉት፡፡ እውነትን መቀበል ቢከብድም ይጋፈጡት፡፡ ያኔ ጥሩ ይሆናል፡፡

አበበ ጥበቡ
ዘበኛ ሠፈር፣ አዲስ አበባ